የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ ጥር ፳ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 11
ADDIS ABABA 28th January 2011

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፩፻፺፯/፪ሺ፫

የኢትዮ-ቴሌኮም ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ……………………………………ገፅ ፭ሺ፮፻፺፫

CONTENTS

Regulation No. 197/2010

Ethio-Telecom Establishment Council of Ministers Regulation…………………………………………… Page 5693

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፯/፪ሺ፫

## ኢትዮ-ቴሌኮምን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ በአንቀጽ ፵፯(፩)(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮ-ቴሌኮም ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፺፯/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **መቋቋም**

፩/ ኢትዮ-ቴሌኮም (ከዚህ በኋላ "ቴሌኮም" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ቴሌኮሙ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

፫. **ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን**

በመንግሥት የሚሰየም አካል የቴሌኮሙ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል፡፡

፬. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የቴሌኮሙ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ሊኖረው ይችላል፡፡

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 197/2010

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIO-TELECOM

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 47(1)(a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethio-Telecom Establishment Council of Ministers Regulation No. 197/2010".

2. **Establishment**

1/ The Ethio-Telecom (hereinafter the "Telecom") is hereby established as a public enterprise.

2/ The Telecom shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. **Supervising Authority**

A body to be designated by the government shall be the supervising authority of the Telecom.

4. **Head Office**

The Telecom shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

ያንዱ ዋጋ
Unit price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.box 80,001

**፭. ዓላማ**

ቴሌኮሙ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

፩/ በቀጣይ ትውልድ ኔትወርክ ቴክኖሎጂ ላይ ተመስርቶ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎትን መስጠትና ማዳረስ፤

፪/ የሚቀጥለው ትውልድ ኔትወርክ ቴክኖሎጂ ላይ ተመስርቶ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴሌኮም አገልግሎት መስጠት የሚችል በዕውቀቱ፣ በችሎታው፣ በሥራ ዝንባሌውና ባህሉ ብቁና ተስማሚ የሆነ የሰው ኃይል መገንባት፤

፫/ የመንግሥት የልማት ፖሊሲና ቅድሚያ ትኩረት መሠረት በማድረግ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችንና ኔትዎርክ ማቋቋም፣ ማካሄድ፣ መጠገንና ማስፋፋት፤

፬/ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የድምጽ፣ የዳታ፣ የቪዲዮ እና ሌሎች ተዛማጅ ተጨማሪ አገልግሎቶችን መስጠት፤

፭/ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ተቀብሎ ማስተላለፍን ጨምሮ በተቀናጀ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመደገፍ የሚሰጡ የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን መስጠት፤

፮/ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሚያወጣውን መመሪያና የፖሊሲ አቅጣጫ መሠረት በማድረግ ቦንድ መሸጥና በዋስትና ማስያዝ እና ከሀገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤

፯/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ::

**፮. ካፒታል**

ለቴሌኮሙ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፵ ቢሊዮን (አርባ ቢሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፳ ቢሊዮን ፪፻ ሚሊዮን (ሃያ ቢሊዮን ሁለት መቶ ሚሊዮን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል::

**፯. የኃላፊነት መጠን**

ቴሌኮሙ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም::

**፰. ቴሌኮሙ የሚቆይበት ጊዜ**

ቴሌኮሙ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል::

**፱. የተሻረ ደንብ**

የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲/፲፱፻፹፱ (በደንብ ቁጥር ፺፫/፲፱፻፺፮ እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል::

**፲. የመብትና ግዴታ መተላለፍ**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲/፲፱፻፹፱ ተቋቁሞ የነበረው የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለቴሌኮሙ ተላልፈዋል::

**፲፩. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከህዳር ፳ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል::

አዲስ አበባ ጥር ፳ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**5. Purposes**

The purposes for which the Telecom is established are:

1/ to provide and make accessible next generation network based world class standard information technology services;

2/ to build a competent next generation network based workforce with appropriate knowledge, skill, attitude and work culture to provide world class telecom service;

3/ to engage, in accordance with development policies and priorities of the government, in the construction, operation, maintenance and expansion of telecommunications networks and services;

4/ to provide domestic and international voice, data, video, and other related value-added services;

5/ to provide communication services using integrated information technology platform, including re-broadcast of television services;

6/ in line with directives and policy guidelines issued by the Ministry of Finance and Economic Development, to sell and pledge bonds and to negotiate and sign loan agreements with local and international financial sources;

7/ to engage in other related activities necessary for the attainment of its purposes.

**6. Capital**

The authorized capital of the Telecom is Birr 40,000,000,000 (forty billion Birr) of which Birr 20,200,000,000 (twenty billion two hundred million Birr) is paid up in cash and in kind.

**7. Liability**

The Telecom shall not be held liable beyond its total assets.

**8. Duration**

The Telecom is established for an indefinite duration.

**9. Repealed Regulation**

The Ethiopian Telecommunication Corporation Establishment Council of Ministers Regulation No. 10/1996 (as amended by Regulation No. 93/2003) are hereby repealed.

**10. Transfer of Rights and Obligations**

The rights and obligations of the Ethiopian Telecommunication Corporation established under the Council of Ministers Regulation No. 10/1996 are hereby transferred to the Telecom.

**11. Effective Date**

This Regulation shall come into force on the 29th day of November, 2010.

Done at Addis Ababa, this 28th day of January, 2011.

**MELES ZENAWI**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት